በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርስቲ
አዲስ አበባ - ኢትዮጵያ
Federal Democratic Republic of Ethiopia
Ethiopian Civil Service University
Addis Ababa – Ethiopia

ቀን: March 04, 2016

ቁጥር:

ለሁሉም ካልኦትና ኤና ኮሌጂ መምህራን ሠራተኞች የተላከ

ጉዳዩ፣ በ2016 የትምህርት ዘመን በ2ኛ ዲግሪ በመደበኛ መርሀግብር ወደ ዩኒቨርሲቲያችን የሚገቡ ዕጩዎችን ይመለከታል፡፡

ዩኒቨርሲቲያችን በ2016 የትምህርት ዘመን በማስተርስ ዲግሪ ተቀብሎ የሚያስተምራቸው ዕጩዎችን ለመምረጥ ግንቦት 5 እና 6 ቀን 2015 ዓ.ም የመግቢያ ፈተና መስጠቱ እና በዚሁ መሠረት በክረምት መርሀግብር ለመማር ከተወዳደሩት መካከል የተመረጡትን ዕጩዎች ከዚህ በፊት አሳውቀናችሁ እንደነበር ይታወሳል፡፡ ሆኖም የምልመላ ውጤቱን ካሳወቅናችሁ በኋላ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ የትምህርት ሚኒስቴር በተሰጠው መመሪያ መሠረት የ2015 የክረምት ትምህርት ፕሮግራም ተሰርዟል፡፡

ዩኒቨርሲቲያችንም ይህንኑ ግምት ውስጥ በማስገባት በሚ/ስቴር መ/ቤቱ በተሰጠ ውሳኔ ምክንያት የክረምት ትምህርት ፕሮግራም የተሠረዘባቸውን ተማሪዎች ለመደበኛው ፕሮግራም ከተፈተኑት ጋር በማወዳደር የተሻለ ውጤት ያስመዘገቡትን ወደ መደበኛ ፕሮግራም አዛውሮ ለማስተማር ወስኗል፡፡ በዚሁ አግባብ በመደበኛው መርሀ ግብር ለመማር ተወዳድረው የተመረጡትን እና ከክረምት ትምህርት መርሀ ግብር ወደ መደበኛው መርሀ ግብር እንዲዛወሩ የተፈቀደላቸውን በድምሩ የ_____ ዕጩዎችን ስም ዝርዝር የያዘ _____ገፅ ከዚህ ደብዳቤ ጋር አባሪ አድርገን ልከናል፡፡ በዘሁ መሠረት፣

1. **የምዝገባ ቀን፡- መስከረም 28 ቀን 2016 ዓ.ም ብቻ ይሆናል፤**
2. **የምዝገባ ቦታ፡ ሲኤምሲ በሚገኘው በዩኒቨርሲቲው ዋና ግቢ በር ቁጥር- 3 ሬጅስትራር ጽ/ቤት ውስጥ ይሆናል፤**
3. **ዕጩዎች ለምዝገባ ሲቀርቡ የሚከተሉትን መያዝ ይጠበቅባቸዋል፣**
   - 3.1. ሁለት ጉርድ ፎቶ ግራፍ፣
   - 3.2. ከሚሰሩበት መሥሪያ ቤት በአድራሻ ለዩኒቨርስቲያችን ውጤቱ ከተገለጸ በኋላ የተፃፈ የድጋፍ ደብዳቤ፣
   - 3.3. ዋናዎቹን (Original) የመጀመሪያ ዲግሪና የውጤት ማስረጃ (Student Copy)፣
   - 3.4. የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን ካገኙበት የከፍተኛ ትምህርት ተቋም Official Transcript ለዩኒቨርስቲያችን በፖስታ ሣጥን ቁጥር 5648 አስቀድመው የላኩበት ማስረጃ፣
   - 3.5. የሴምስተር ክፍያ ብር 400.00 (አራት መቶ ብር) በዩኒቨርስቲያችን የንግድ ባንክ አካውንት ቁጥር 1000009144181 ያስገቡበት የባንክ ስሊፕ፣

ከሠላምታ ጋር

ለማ ቡቃ አንገሳ (ዶ/ር)
የአካዳሚክ ፕሮግራሞች ፕሮዘደንት

ማሳሰቢያ፡-

1. ዕጩዎች የሚመዘገቡት በግንባር ሲቀርቡ ብቻ ነው፡፡
2. ኦፊሻል ትራንስክሪፕት አስቀድሞ ወደ ዩኒቨርስቲው ያላስላከ ማንኛውም አዲስ ተማሪ መመዝገብ አይችልም፡፡
3. ተማሪዎች የራሳቸውን ብርድ ልብስ እና አንሶላ መያዝ ይጠበቅባቸዋል፡፡
4. በወቅቱ ቀርቦ ባልተመዘገበ ተማሪ ምትክ ሌላ ተጠባባቂ እንደሚጠራ ታውቆ ከምዝገባው ቀን አስቀድሞም ሆነ ዘግይቶ ለሚመጣና ከተወዳደረበት ውጪ የዲፓርትመንት ለውጥ ጥያቄ የሚያቀርብ ዕጩ አይስተናገድም፡፡

እንዲያውቁት፡-

- ለፕሬዝዳንት ጽ/ቤት

ግልባጭ፡-

- _____ ኮሌጅ
- ለተማሪዎች አገልግሎት ዳይሬክቶሬት
- ለቤተመጽሐፍትና መረጃ ማእከል ዳይሬክቶሬት
- ለድህረ ምረቃ ት/ቤት ዳይሬክቶሬት
- ለአካዳሚክ ፕሮግራሞች ዳይሬክቶሬት
- ለዋና ሬጅስትራር

ኢ.ሲ.ሰ.ዩ

☎ ስልክ 0116 46 30 15 Operator 0116 46 30 12 President 0116 46 30 13
(Tel) 0118 33 31 86 Admission Office 0118110836 External Relations Off. 0116 46 23 44 ቴሌ ፋክስ (Fax) 0116 46 30 16
Website:www.ecsu.edu.et E-mail:ecspro@ecsc.edu.et ✉ P.O.Box ፖ.ሣ.ቁ. 5648